# <u>አምቦ ወይስ አምስተርዳም?</u>

## <u>(ጉድ ነው ተቃዋሚ!!)</u>

ከሽመልስ በየነ

አንድ ድረ-ገጽ ሰሞኑን ስቃኝ ዶክተር መራራ ጉዲና የተባሉት የተቃዋሚ ድርጅት መሪ ወደ ሆላንድ መዝለቃቸውንና መጪው እሁድም በአምስተርዳም ነዋሪ ለሆኑ ኢትዮጵያውያን ስለ ኢትዮጵያ ሁነታ ገለጻ እንድሚሰጡ አነብብኩ። ዓይኔን ማመን አቃተኝ--ዶክተሩ ወደ አምቦ መሄድና ሕዝብን መቀስቀስ ትተው ወደ ሆላንድ - ያውም <u>ለሶስት ወር</u>! — ምን አመጣቸው? ዶክተር መረራ ምነዋ በሀገራችን ወሳኝ ጉዳዮች ብቅ ሲሉ ትምህርት-- ስራ እያሉ በተለይ ወደ ሆላንድ እየሄዱ የሚቆዩት? ምነዋ የአምቦ ውሃ እየመረረ መምጣት ሲከጅለው፣ በማይጎረብጠው የአምሰተርዳም ውሃ ማለስለስ ፈቀዱ?

የሀገራችን ህጋዊ ተቃዋሚ ድርጅቶች ተኪ የለሽ ሆነው 100% ግለሰብ መሪዎች በብቸኝነት ድርጃ ተሰይመውባቸው ያሉ መሆናቸ ይታወቃል። ሹሞቹ ከሌሉ ደካማዋም ስራ ታበቃለች። በቱኒዝያ ተጀምሮ ወደ አልጄሪያ፣ ግብጽ፣ የመን፣ ጆርዳንና ወደ ጋቦንም እየተሰራጨ ያለው ሕዝባዊ ትግል ኢትዮጵያንም ይዳሥሥ ብለው የሚመኙ ዜጎች ሁሉ ምንም እንኳን እነዶክተርና ኢንጂነር ተቃዋሚ ሳይሆኑ ተባባሪ መባል የሚገባቸው ቢሆኑም ባለው ከባድ ቀውስ የተነሳ በመጠኑ ወይም በለሆሳስም ቢሆን ተቃውሞን ያስሙ ይሆን፣ ሕዝቡን ተነስ ይሉ ይሆን ብሎ ተስፋ ያደረጉ አልጠፉም። ወይ ነዶ ሆኗል እንጂ የእኛ ነገር። ዶኮተር መረራ ወደ ሆላንድ መጥቶ መደበቁንና ቅስቀሳ ለማያስፍልገው ወገን ቅስቀሳ መስጥትና በዚያውም የለምደችባቸውን "ስንቅ' መጠየቁን መርጠዋል። ኢንጂነሩ በእርስ በርስ ንትርክ መጠምዱን መርጠዋል። አቶ ስዬም ዘጠኝ ዓመት ከኖርኩብት ቤት

ልባረር ነው ሲል እንጂ ተነሱ ክተቱን ሲጮህ አልተሰማም። ዶክተር ነጋሶም ቢሆኑ የቤቴ ቆርቆሮ እያፈሰሰ ነው እንጂ ሕዝባዊ ትግሉን ለማፋፋም ጥሪ አላቀረበቡም። ኢሕአፓም ሲሽረሽረው ከነበረው አንጃ ተላቆ አለሁ ከጎናችሁ ማለትን ቢጀምርም የተነሱ ጥሪውን በተጨባጭ ትግሉን በመምራት ሊያጅብ መቻሉ አጠራጣሪ ነው። በሻዕቢያ እርዳታ ትጥቅ ትግል እናካሂዳለን ያሉትም ክፍሎች በንትርክ ላይ ናቸው። ይህ እንግዲህ የሀገራችንን ሁኔታ ከቱኒዝያ የተለየ ያደርገዋል።

አንዳንድ ፀሐፊዎችና ተናጋሪዎችም በድረ-ገፆችና በፓልቶክ የመነጋገሪያ ክፍሎች እንደቱኒዝያና ሌሎቹ ሀገሮች ሕዝቡ ቢነሳ ወያኔ ይጨፈጭፈዋል ሲሉ አስነብበውናል ወይም አስደምጠውናል። የወያኔን አረመኔነት ማስረገጥ አንድ ነገር ነው። ይህን ፀባዩን እንደ ማስፈራሪያ ማቅረብ ግን ስህተት ይሆናል። ዱሮውንም ወያኔ አፋኝ ባይሆን ኖሮ ህዝባዊ አመጽ ባላስፈለገ ነበር። በሕዝብ ፈቃድ የስልጣን ሽግግር የሚቻል ቢሆንማ ኖሮ፣ ትግሉ አልጋ በአልጋ በሆነ። በሰሞኑ ሕዝባዊ አመጽ ሌሎች ሕዝቦች እያስመዘገቡት ያለው ድልም ቢሆን ያለመስዋዕትነት እየተገኘ አይደለም። የሀገራችን ሕዝብም በተገቢው ድርጅታዊ ብቃት ከተመራ የመስዋዕትነት ዋጋ ለመክፈል እንደማይገደው አስመስክሯል። በቅርቡ እንኳ በ1997 ዓ. ም.።

ከቱኒዝያ ተነስቶ በብዙ ሀገሮች አምባገነኖችን እያጥለቀለቀ ያለው ሕዝባዊ እምቢታ ግን የወያኔን ፈቃድ አግኝተው የሚሰሩትን ተቃዋሚዎች እኛም ቤት እሳት አለ አላሰኛቸውም። በልጅግ አሊ እንዳስቀመጡት በሰላማዊ ትግል ሳይሆን በሰላማዊ እንቅልፍ ላይ ናቸው - እንደተለመደው። ለእነሱ ገና እኩለ ሌሊት ነው። የሚጥም እንቅልፍ የሚከሰክሱበት። ስለሌሎቹ ሀገሮች አመጽ መስማታቸውም ያጠራጥራል - ከልባቸው። እሌሎቹ ጋር ንጋትን ለመውለድ ምጥ የተያዘችው የጠዋት ፀሐይ ወጋገን በብልጭታም አልታየቻቸው። እንኳንስ በተግባር በመግለጫም ደረጃ ቃልም አልተነፈሱም።

ያው የወያኔ ዳግም መጨነሊያ ድግስ — ምርጫ — ሲመጣ ብቅ ይላሉ። ኮካ ቤት ከተባለ ፍሪጂም ቤት ነው እንዳለችው፣ ለእነሱም ያው ሥራ አይደል። ምርጫ ቦርድ የሥራ ሰዓት ደረሰ ደወሉን ሲደውል ከእንቅልፋቸው ይነሳሉ። ወያኔ ሥልጣን እንደያዘ ከዲፓርትመንት ሃላፊነት አንስቶ የሳይንስና ቴክኖሎጅ ምክትል ኮሚሽነር ካደረጋቸው በሁዋላ አዲሱ ፍቅራቸው ሲያበቃና ሲያንሳፍፋቸው፣ ተቃዋሚ ነኝ ያሉትም ግዛቸው ሽፈራው ሰሞኑን ያረጋገጡልን ይህንኑ ነው። ወያኔ ቆጥሮ የሚፈቅድልን ጊዜ ጠብቀን ወረግቡ እንሆናለን ነው ያሉን። ለምርጫ ተወዳደሩ ሲላቸው በተቃዋሚነት ሊወዳደሩ። ከእንቅልፋቸው ተነስተው ሕዝብና ምጥ ሊያሲዙ። ከዚያም ቀድሞውንን ምርጫው ውጤቱ በወያኔ አሸናፊነት፣ እነሱም በአጃቢኒት ነውና የተዘጋጀው፣ ሕዝብ የፀነሰውን ድል ሊያስጨነግፉ።

የሀገራችን ሰው፣

መራኸር ተኳሸሰን እኛ ስናውቀው፣
ዝናር በቂጤን ማንደባለቀው?

እንዳለው ነውና፣ ማነው የምር ተቃዋሚ? ማነው መስዋዕት ከፍሎ፣ መስዋዕት ከፍለን፣ መርቶ ለድል ሊያበቃን የሚችል ብለን የምንጠይቅበት የፈተና ወቅት ላይ ያለን ይመስለኛል።